# የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት

## የሙኒክ ደበረ ብሥራት ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ « ለሥራ ከመትጋት አትለግሙ» ሲል ለሮሜ ሰዎች የመከራቸውን መንሥኤ በማድረግ በአሁኑ ጊዜ በሙኒክ ከሚኖሩት ወደ 2500 ይደርሳሉ ተብሎ ከሚገመቱት ኢትዮጵያውያን መካከል በደብረ ብሥራት ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ሥር የሰበካ ጉባኤ ቅጽ ሞልተው የተመዘገቡ ምዕመናን ብዛት 506 ያህል ሲሆን የአሥራት አስተዋጽዖ በማድረግ ላይ ያሉ ምዕመናን ግን 147 ብቻ ቢሆኑም ሰበካ ጉባዔው ዓላማውን ለማስረዳት ጥረት እያደረገ ነው ።

አገልግሎት የሚሰጠውም በዕለተ ሰንበት በወር ሦስት ጊዜ ቅዳሴ ያለ ሲሆን በኑርንበርግም በወር አንድ ጊዜ እሑድ የሥላሴን በዓል ምክንያት በማድረግ ቅዳሴ ይቀደሳል ። ምንም እንኳ የራሳችን ቤተ ክርስቲያን ገና ለመሥራት በጥረት ላይ ብንሆንም በጥገኝነት ባለንበት ቤተ ክርስቲያን ጸሎቱና ቅዳሴው በየጊዜውና በየበዓላቱ ሳይታጎል በመከናወን ላይ ይገኛል። ከአገልግሎቶቹም ዋና ዋናዎቹ የክርስትና የጋብቻ የፍትሐትና ስብከተወንጌል ሲሆኑ እንደ አስፈላጊነቱ ሌሎች የማሕበራዊ ዘርፎችንም በማካተት አገልግሎት ይሰጣል ። የሙኒክ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በባደን ቩተንበርግና በኑርንበርግ ያሉትንም አጥቢያዎች አጣምሮ ሲመራ ከቆየ በኋላ አሁን በአሽቱትጋርት ካህን በመገኘቱ እራሱን በመቻል ላይ ሲሆን በመጪው ግንቦትና ሰኔ አካባቢ በይፋ እንደሚመረቅ ይጠበቃል ። የኑርንበርግም ለሐምሌ ሥላሴ ይመረቃል ።

በዕቅዱ መሠረት ያከናወናቸውን የሥራ እንቅስቃሴዎች በአጭሩ እንደሚከተለው እንመልከታለን ። ቅዱስ መጽሐፍ እንደሚያዘው ለእግዚአብሔር አሥራት ማውጣት የሃይማኖት ግዴታ ነውና ቤተ ክርስቲያናችን በየጊዜው ይህን በማስተማሯና እንዲሁም የሰበካ ጉባኤው ተጠናክሮ የዓባላትን ምዝገባና አሥራት አወጣጥ በሥርዓት መምራት በመጀመሩ እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁንና ገና ብዙ ቢቀርም ከበፊቱ አሁን ጥረቱ ውጤት አልባ አልሆነም ።

<u>ክርስትናን በተመለከተ :-</u>

በደቡቡ ክፍለ ጀርመን አገልግሎት መስጠት ከተጀመረበት ከ፲፱፻፹፬ ዓ.ም ( 1992)ጀምሮ በርከት ያሉ ሕጻናት በአጠቃላይ በባየርና በባደንቩተንበርግ እስከ አሁኑ ዓመት ፲፱፻፺፭ ሚያዝያ ወር ( 2003 ) ድረስ 336 ሕጻናት የተጠመቁ ሲሆን ቤተ ክርስቲያኒቱ እነዚህን ሕጻናት የሀገራቸውን ቋንቋ እንዲያውቁ ለማድረግ የትምህርት ፕሮግራ ምአውጥታ ለወላጆች ባደረገችው ጥሪ መሠረት ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት የሚልኩ ወላጆች ጥቂት ቢሆኑ ምበመጡት ትምህርቱ ተጀምሮ በመስጠት ላይ ይገኛል። በእርግጥ ወላጆች ሥራ ሊበዛባቸውና ፕሮግራማቸው




የተጣበበ ሊሆን ይችላል ቢሆንም ቤተክርስቲያን ከኅናቸው እስከቆመች ድረስ ልጆቻቸውን ፊደል ማስቆጠር በሃይማኖትበግብረ ገብነት ተኮትኩተው እንዲያድጉ ማድረግ የቤተ ክርስቲያን ድርሻ ጭምር ቢሆንም የወላጆችም ኃላፊነት ታክሎበት ቤተ ክርስቲያን ላወጣችው መርሐ-ግብር በመታዘዝ ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲያመጡ አሁንም ጌታችን «ሕጻናትን ተዋቸው ወደ እኔም ይመጡ ዘንድ አትከልክሏቸው» ማቴ.፲፱፥፲፬ ያለውን በማስገንዘቧ በተጀመረው ፕሮግራም ጥሩ ውጤት እየተገኘ ነው ።

በአሁኑ ጊዜ ትምህርታቸውን የሚከታተሉ ሕጻናት ብዛት 12 ሲሆኑ በየሳምንቱ ቅዳሜና መደበኛ ትምህርታቸው ሲዘጋ በሚሰጣቸው ትምህርት መጻፍና ማንበብ በፍጥነት በመቻል ላይ ሲሆኑ ተሳትፎአቸው እንዲጠናከርና የቤተ ክርስቲያኒቱ አካልም ሆነው እንዲያድጉ በመንፈሳዊ በዓላትና በሙኒክ በሚከበረው የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቀን ላይ ልዩ ልዩ ፕሮግራሞችን በማቅረብ ምዕመናኑን በማነቃቃት የተማሩትን በተግባር በመግለጽ ላይ ይገኛሉ ።

ጋብቻን በተመለከተ :-

እስከ አሁን ድረስ ጋብቻቸውን በቤተ ክርስቲያን በሥርዓተ ተክሊል የፈጸሙ ጸ፰ ወጣቶች ናቸው። ወጣቶች ከክርስትና ጋር ግንኙነት በሌለው ልማድ በመመራት ከክርስቲያናዊ ሥርዓተ ጋብቻ ቅዱስ ቊርባንን በመሸሽ ብዙም ተሳትፎ ሲያደርጉ አይታዩም ። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን ለምእመናን ስለሥርዓተ ጋብቻ ባለማቋረጥ ትምህርት በመስጠት ላይ ትገኛለች ።

የደብረ ብሥራት ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ ጽሕፈት ቤት የበላይ ሆኖ የሚመራቸው የአገልግሎት ዘርፎች የሚከተሉት ናቸው ።




ሰንበት ትምህርት ቤት :-

ካህኑ በማይገኙበት ዕለተ ሰንበት ምዕመናን ትምህርተ ወንጌል ሰምተው ተምረውና እግዚአብሔርን አመስግነው የሰንበትን በረከት እንዲቀምሱና እንዲሁም መዘምራን ከቅዳሜ የጥናት ፕሮግራማቸው ሌላ ምእመናን በዝማሬ ላይ ተሳትፎ እንዲኖራቸው እያደረጉ ሲሆን በተጨማሪም በሰንበት ትምህርት ቤቱ ሥር የሕጻናት ክፍል ስላለ ቅዳሜ ቅዳሜ ከ16 ሰዓት እስከ 18 ሰዓት ድረስ ማንበብና መጻፍ ግብረገብ መዝሙር እንዲማሩ በማድረግ አገልግሎት በማበርከት ላይ ይገኛል ::

የምግባረ- ሠናይ ክፍል :-

የተፈጥሮ አደጋን በሚመለከት ባለፈው በሀገራችን ድርቅ ደርሶ በነበረበት ጊዜ እርዳታ ለማሰባሰብ ተቋቁሞ የነበረው ኮሚቴ ዓላማውን ግብ በማድረሱ በዚሁ ከሚበተን ወደ ምግባረ ሠናይ ቋሚ ኮሚቴነት ተቀይሮ በሰበካ ጉባኤው ዘርፍነት እንዲሠራ የተወሰነ ሲሆን ይኸው ኮሚቴ አሁንም በሀገራችን ላይ በደረሰው የድርቅ አደጋ ከሀገራችንም ሆነ ከእናት ቤተ ክርስቲያናችን በኩል ለጀርመን የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ባደረገችው ጥሪ መሠረት ለእርዳታ የሚሆን ገንዘብ በማሰባሰብ ላይ ይገኛል ::

የማእከል አሠሪ ኮሚቴ :-

በሰበካ ጉባኤው ዘርፍነት የቤተ ክርስቲያናችንን አገልግሎት የሚያግዙ ኮሚቴዎች ከሚያከናውኗቸው አገልግሎቶች መካከል የቤተ ክርስቲያናችንን ማእከል ለማሰራት የተመሠረተው ኮሚቴ አንዱ ነው :: ይህም ኮሚቴ ዕቅዱ እስኪፈጸም ያላሰለሰ ጥረት እያደረገ ነው በዓባላት አስተዋጽዖ ላይ ብቻ ሳያተኩር የተለያየ ‑ገቢ የሚያስገኙ ዕቅዶችን በማውጣት የገቢ ማስገኛ ምንጩን ከፍ በማድረግ ላይ ይገኛል ። "ታሪክ ማውራት የሚቻለው የራስንም ታሪክ በመሥራት ሲሆን ደግሞ የበለጠ ማንነትን ይገልጸል። መተባበር የብዙ ነገር መገኛ ነው በቀላሉ የእጆቻችንን ጣቶች ብንመለከት ቆርሰን ለመመገብ ከትንሹ እስከ ትልቁ ሲተባበሩ ስናይ ከተፈጥሮ መማር እንዳለብን እንገነዘባለን እጣቶች ሙሉ ባይሆኑ ምን ማድረግ ይቻላል ከዚህ አንማርም ለእግዚአብሔርስ ቤት ቅንዓት አያነሳሳንም ስለሃይማኖታችንስ አንቀናም እስቲ እናስብበት የእግዚአብሔርን ማደሪያ ቤት ለመሥራት ምንያህል ጊዜ እንደተጓዝን እንመልከት በአጭሩ ብንተባበር ግን ይህንን ያህል ጊዜ ባልወሰደብን ነበር" በማለት የማእከል አሠሪ ኮሚቴ የሚያደርገውን እንቅስቃሴ የኮሚቴው ዋና ጸሐፊ በአንድ ወቅት ለመግለጽ እንደሞከሩት ሁኔታው የሚያሳየው የአሠሪ ኮሚቴው የተጣለበትን ኃላፊነት እና የተረከበውን አደራ ማለትም የታቀደውን ማእከል አሠርቶ በዐይኑ እስከ ሚያይ ድረስ ዕረፍት የሌለው መሆኑንንና ይህም ለቤተ ክርስቲያናቸው ቀናኢነት ያላቸውን ምእመናን ቁርጠኛነትም ያሳየናል :: ስለዚህም በሥራ ላይ ያለው ሁለተኛው የቤተ ክርስቲያኑ ማእከል አሠሪ ኮሚቴ ከተመረጠበት እ.ኤ.አ ከጥር ፲፱ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓመተ ምሕረት ጀምሮ በተቻለው አቅም ከምእመናኑ ጋር በመተባበር የሚጋነን ባይሆንም በእኛ እምነት የተለያዩ የገቢ ምንጮችን በመፍጠር የእግዚአብሔር ስሙ የተባረከ ይሁንና አጥጋቢ ውጤት ኢያስመዘገበ ይገኛል። የማእከሉ አሠሪ ኮሚቴም በየጊዜው መደበኛ ስብሰባ እየተሰበሰበም ንግግር ብቻ ሳይሆን የተለያዩ ሀሳቦችን እያመነጨ ይመክራል የወሰነውንም ይተገብራል። ከነዚህም ተግባራት አንዱ ብዙዎቹ የሰበካው ነዋሪዎች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የተሳተፉበት ስለሆነ የታወቀ ነው ይህም የዕለተ ሰንበት ማለትም የእሑድ እሑድ ከጸሎት በኋላ የመገናኛ ክፍለ ጊዜ እንዲሆን በመወሰኑ ከ13 ሰዓት እስከ 19 ሰዓት ባለው ጊዜ ልዩ ልዩ የምግብ ዓይነቶችን እያዘጋጀ ያቀርባል :: ይህም በበጎ አድራጊዎች የሚቀርብ ሲሆን ለበረከቱ ያልታደሉም ካሉ አሁንም ዕድሉ ስላለ እንቀራረብና የበረከቱ ተሳታፊዎች እንሁን በማለት አሠሪ ኮሚቴው ጥሪውን ያስተላልፋል ።



በዚህ አጋጣሚ ለዚህ ተግባር መሳካት አስተዋጽዖ ላደረጉ በማድረግም ላይ ላሉ እንዲሁም ለማእከል ማሠሪያ ገንዘብ በማሰባሰብ በኩል ባለማቋረጥ አብረውን ለሚደክሙ ምእመናን እኅቶቻችንና ወንድሞቻችን ሁሉ በቅድሚያ ከሁሉም በፊት በመልአኩ በቅዱስ ገብርኤል ስም ምስጋናችን እጅግ ከፍ ያለ ነው እንላለን «ድር ቢያብር አንበሳ ያሥር» ነውና ።

ከቤተ ክርስቲያኑ ሰበካ ጉባዔ አስተዳደር ጋር በመተባበር በ፲፱፻፺፱ ዓ.ም ለታኅሣስ ገብርኤል ዋዜማ ዲያቆን ደጀኔ ሽፈራው መጥቶ ያስተማረውን መንፈሳዊ ትምህርት ድምጽና ምስሉን በመቅረጽ ትምህርቱን ላልሰሙት እንዲሰሙት ለሰማነው በየጊዜው እንድንማርበት በአምስት የተለያዩ ርዕሶች አምስት ካሴቶች አዘጋጅተን በገበያ ላይ በማዋል ሌላ የገቢ ምንጭ እንዲኖር አድርገናል ።

በዓመት ሁለት ጊዜ ቅዱስ ገብርኤል ይከበራል በዚህም በዐል ጥላ በማዞር በዓሉን ሊያከብሩ የመጡ ተሳላሚዎች ምእመናን የገንዘብ ስጦታ እንዲያደርጉ ይማጸናል ይህም ሌላው የገቢ ምንጭ ነው። «እግዚአብሔር በደስታ የሚሰጠውን ይወዳልና እያንዳንዱ በልቡ እንዳሰበ ይስጥ በኀዘን ወይም በግድ አይደለም።» ፪ኛ ቆሮ. ፱÷፯ «በእናንተ ዘንድ ያሉ በልባቸው ጥበበኞች የሆኑ ሁሉ መጥተው እግዚአብሔር ያዘዘውን ሁሉ ያድርጉ ማደሪያውን ድንኳኑን.....ይሥሩ» ይለናል የእግዚአብሔር ቃል ዘፀ.፴፭÷፲-፳፱ ።

ከዚህ በላይ ያሉት ጥቅሶች እንደሚያስረዱን ሕዝበ እስራኤል በሙሴ መሪነት የእግዚአብሔርን ማደሪያ እንዴት አድርገው እንደሠሩት አንብበን መረዳት እንችላለን ።

«እግዚአብሔርም አለው በፊቴ የጸለይከውን ጸሎትህን ልመናህን ሰምቻለሁ ለዘለዓለም ስሜ በዚህ ያድር ዘንድ ይህን የሠራኸውን ቤት ቀድሼዋለሁ ዓይኖቼና ልቤም በዘመኑ ሁሉ በዚያ ይሆናሉ ።» መጽ.ነገ.ቀዳ.፱+፫ ። ስለዚህ የንጉሥ ሰሎሞንን አርዓያ በመከተል አባቶቻችን ለእኛ ለልጆቻቸው ታላላቅና ድንቅ የሆኑ አብያተ ክርስቲያናትን በዘመናቸው ሠርተው አቆይተውናል እኛም የአባቶቻችንን ፈለግ ተከትለን እንደሆንና ምን እያደረግን እንዳለን እያንዳንዳችን እራሳችንን እንመርምር ።

በአጠቃላይ የሁሉም ሩጫና ግብ የእኛ የራሳችን የሆነች ቤተ ክርስቲያን በዚች በሙኒክ ከተማ ማቋቋም በመሆኑ ይኸው እንዲሳካ በዓመት አንድ ጊዜ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቀን በሚል በዓል በማዘጋጀት ምእመናንን ለማቀራረብ እንዲሁም ከጀርመኖቹ ጋር ለመቀራረብና የገቢ ምንጭም ማግኛ እንዲሆን ስናከብር እነሆ ይህ ዓመት አምስተኛ ጊዜ ይሆናል ።

## የጽዋ ማኅበራት :-

በጥሩ ሥራቸው ለሰዎች በምሳሌነት ከሚጠቀሱ ማኅበራት መካከል በጌታ በቅዱሳን በመላእክት ስም በምእመናን ኅብረት የሚመሠረቱ የጽዋ ማኅበራት እንደሆኑ የሚታወቅ ሲሆን ይኸንኑ ጥሩ ምሳሌነት መሠረት በማድረግ በሙኒክ ደብረ ብሥራት ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ሥር ከተመሠረቱትና በጎ ተግባራት በማከናዎን ላይ ከሚኙት ማኅበራት መካከል የቅዱስ ገብርኤል ና የኪዳነ ምሕረት ጽዋ ማኅበራት ቅድሚያ ቦታ ይይዛሉ ።

ማኅበራቱ ከተመሠረቱ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ በርካታ ጠቃሚ ተግባራትን ያከናወኑ ሲሆን የማኅበራቱ አባላት ብዛትም የገብርኤል ፳፬ የኪዳነ ምሕረት ፵፬ ይደርሳል ። የማኅበራቱ ዋና ዋና ዓላማዎች ከዚህ የሚከተሉት ናቸው ።

1. በየወሩ በእምቤታችንና በመልአኩ ስም እየተሰበሰቡ እግዚአብሔርን አመስግኖ ጽዋ መቅመስ ፤
2. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ሥርዓት መጠበቅ ፤
3. ከደብረ ብሥራት ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር የሚወጡ መመሪያዎችን ማክበር፤
4. በማኅበሩ አባላት መካከል ክርስቲያናዊ ወንድማማችነትና እኅትማማችነት እንዲሰፍን ማድረግ ይህም ማለት በደ ስታም ጊዜ ሆነ በሀዘን ወቅት የማኅበሩ አባላት እርስ በርስ እየተደጋገፉ እንዲኖሩ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ፤

5.የጽዋ ማኅበራቱን ዓባላት ቁጥር ከፍ ለማድረግ እንዲረዳ የማኅበራትን ጠቃሚነት በተግባር እያሳዩ አዳዲስ አባላትን ከም እመናን የማኅበሩ አባል ለመሆን ሲያመለክቱ መቀበል ፤
6.በኢትዮጵያ ውስጥ በተለይም በገጠር አካባቢ ለሚገኙ አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት ከደብረ ብሥራት ቤተ ክርስቲያን ጋር በመመካከር እርዳታ ማሰባሰብ ፤
7.የጽዋ ማኅበራቱ መንፈሳዊ እንደመሆናቸው መጠን የተለያዩ መንፈሳዊና ከቤተ ክርስቲያኗ አቋም ጋር የማይቃ ረኑ ማሕ በራዊ ጉዳዮችን በጋራ ለማከናወን በቤተ ክርስቲያኗ ሥር ተመሥርተው በመንቀሳቀስ ካሉ ልዩ ልዩ ኮሚቴዎች ጋር በ ጋራ አገልግሎት የሚያከናውኑበትን ሁኔታ ማመቻቸት ፤
8.በቤተ ክርስቲያኒቱ የልማት እንቅስቃሴ ውስጥ በተቻለ መጠን ተሳትፎ ማድረግ ሲሆኑ እነኝህን ዓላማዎችም በሥራ ላይ ለማዋል የጽዋ ማኅበራቱ ባደረጉት ጥረት ከዚህ በታች የሚጠቀሱትን ተግባራት አከናውነዋ ል ።

ሀ. በአገር ቤት በተለይም በገጠሪቱ ኢትዮጵያ የፈረሱ አብያተ ክርስቲያናትን ለማስጠገኛ ማኅበራቱ ገንዘብ በመላክ ድጎ ማ አድርገዋል ።

ለ. በሙኒክ ሊሠራ ለታቀደው የቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን የገንዘብ እርዳታ ለግሰዋል ።

ሐ. የሞት አደጋ በጽዋ ማኅበር ዓባላት ቤተ ዘመዶች ላይ ከደረሰ በቅርብ በመሆን ከማጽናናትም አልፎ የገንዘብ እርዳታ ይለግሳሉ ።

መ. በሀገራችን አሰቃቂ ድርቅ ገብቶ በነበረበት ወቅት የደብረ ብሥራት ቅደስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን አስ ተዳደር እርዳታ ባሰባሰበበት ወቅት የጽዋ ማኅበራቱ ለድርቅ የገንዘብ እርዳታ አበርክተዋል በአሁኑም ጥሪ ቀጥታ ተሳታፊ በመ ሆን አስተዋጽዖ በማድረግ ላይ ናቸው ።

ሠ. በጽዋ ማኅበራቱ አባላት መካከል ማኅበራዊ ግንኙነቶች እየጠበቁ እንዲሄዱ ለማድረግ አባላቱ ጋብቻ ሲፈጽሙ ልዩ ስጦታ እያዘጋጁ ያበረክታሉ ።

ሰ. የጽዋ ማኅበራቱ በዓመት ሁለት ጊዜ በሚከበረው የቅዱስ ገብርኤል በዓል ከዋዜማው ጀምሮ በኅብረት በመሆን ምዕመናኑን በ ማስተባበር በዋዜማውና በዕለቱ ለምእመናን ጸበል ጸዲቅ በማዘጋጀት ያስተናግዳሉ ::

__ሰሚናር :-__

ተምሮ ማስተማር በሚል መርሐ- ግብር መሠረት የአጥቢያ ቤተ ክርስያናችን ለአራት ጊዜ ሰሚናር አዘጋጅታ ነበር :: ሰ ሚናሮቹም የተካሄዱባቸው ቦታዎች :-

1 . በሙኒክ በ፲፱፹፰ ዓ.ም ፤
2 . በእሽቱትጋርት በ፲፱፻፺ ዓ.ም ፤
3 . በኑርንበርግ በ፲፱፻፺ ዓ.ም ፤
4 . በሙኒክ በ፲፱፻፺፩ ዓ.ም ሲሆኑ በየሰሚናሮቹም የተለያዩ መምህራን ተመድበው በተለያዩ ርእሶች ላይ ትምህርት ሰጥተዋል የሰ ሚናር ተሳታፊዎቹም ከመላው ጀርመን የተሰበሰቡ የቤተ ክርስቲያኒቱ ሰንበት ት/ቤት ተወካዮች ነበሩ ::

__የአብያተ ክርስቲያናት ግንኙነት ( Ökumene ) :-__

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናችን የሙኒክ አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት ( ACKIM)አባል ናት በአባልነቷም አንድጊዜ በማስ ተናገድ የቤተ ክርስቲያኒቱን እንቅስቃሴ ያስተዋወቀች ሲሆን “PHILOXENIA„የተባለውን የኦርቶዶክሳውያን ፤ የካቶሊካውያንና የወንጌላውቦሮንን የወንድማማችነት ኅብረት በቅዳሴና ቀኑን ሙሉ በተከናወነ ፕሮፌሰር ሀየር የተሳተፉበት ውይይትና ገለጻ በማድ ረግ ስለ ቤተክርስቲያናችን ማንነት በማስረዳት ግንዛቤ እንዲኖራቸው ተደርጓል ::

እግዚአብሔር አገልግሎታችንን ይባርክ

በቀሲስ መስፍን ገብረ ማርያም ፈለቀ
የደብረ ብሥራት ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን
አስተዳዳሪ ::